# የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን

## የምርት ገበያ የማዛዘን ወኪሎች የአሠራርና የቁጥጥር

## መመሪያ ቁጥር 543/2013 /እንደተሻሻለው/

# በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን

# የምርት ገበያ የማዛዘን ወኪሎች

# የአሠራርና የቁጥጥር መመሪያ

## መመሪያ ቁጥር 543/2013 እንደተሻሻለው

### የምርት ገበያ የማዛዘን ወኪሎች የአሠራርና የቁጥጥር መመሪያ

### መመሪያ ቁጥር 543/2013 እንደተሻሻለው

በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ማዛዞች ከግብይት ፈጻሚዎችና ከአቅራቢዎች ወክልና ተቀብለው የምርት ርክክብ አገልግሎትን በማከናወን ሥራ ላይ የተሠማሩ የማዛዘን ወኪሎች የሚሰጡትን አገልግሎትና ተጠያቂነታቸውን በህግ በመወሰን አሠራራቸውን በሥርዓት የሚመራ፣ ግልጽ እና ዘመናዊ የግብይት ሥርዓቱን የሚያጠናክር ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 551/1999 (እንደተሻሻለው) አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ (2) ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

**ክፍል አንድ**
**ጠቅላላ**

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የምርት ገበያ የማዘን ወኪሎች የአሠራርና የቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 543/2013 (እንደተሻሻለው)" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡
1) **"ባለሥልጣን"** ማለት በአዋጅ ቁጥር 551/1999 (እንደተሻሻለው) የተቋቋመው የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን ነው፤

2) **"የኢትዮጵያ የምርት ገበያ"** ማለት በአዋጅ ቁጥር 550/1999 (እንደተሻሻለው) የተቋቋመው የምርት ገበያ ነው፤

3) **"ደንብ"** ማለት የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ደንብ ቁጥር 5/2002 ሲሆን በየጊዜው የተደረጉ ማሻሻያዎችንም ይጨምራል፤

4) **"የማከማቻ መጋዘን"** ማለት ማንኛውም በኢትዮጵያ ምርት ገበያ በኩል ለሽያጭ የሚቀርቡ ምርቶችን ተረክቦ ጥራታቸውን በመወሰን በምርት ገበያው ግብይት እንዲካሄድባቸው የሚያመቻች የምርት ማከማቻ መጋዘን ነው፤

5) **"የመጋዘን ተግባራት"** ማለት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ሥር የተመለከቱት በወኪሎች የሚከናወኑ ተግባራት ማለት ነው፤

6) **"አገናኝ አባል"** ማለት በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚጠየቀውን የመመዘኛ መሥፈርት በማሟላት በባለሥልጣኑ ዕውቅና በማግኘት በአባልነት ተመዝግቦ በራሱ ወይም በደንበኞች ስም ግብይት የሚፈፅም ሰው ነው፤

7) **"ተገበያይ አባል"** ማለት በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚጠየቀውን የመመዘኛ መሥፈርት በማሟላት በባለሥልጣኑ ዕውቅና በማግኘት በአባልነት ተመዝግቦ ለራሱ ብቻ ምርት በመግዛት ወይም በመሸጥ ግብይት የሚፈፅም ሰው ነው፤

8) **"ደንበኛ"** ማለት አገናኝ አባል ግብይት የሚፈፅምለት ሰው ወይም አገናኝ አባሉ የግብይት ትዕዛዝ የሚቀበለው ሰው ነው፤

9) **"አቅራቢ"** ማለት በአገናኝ አባል አማካኝነት ምርቱን የሚሸጥ ወይም ለአገናኝ አባሉ የሽያጭ ትዕዛዝ የሚሰጥ ነጋዴ ወይም አምራች ነው፤

10) **"አምራች"** ማለት በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ግብይት እንዲካሄድበት የተወሰነን ምርት በማምረት ለገበያ የሚያቀርብ አርሶ አደር፣ የግል አልሚ ወይም የነዚህ አካላት የኅብረት ሥራ ማኅበር፣ ወይም የመንግሥት የልማት ተቋም ነው፤

11) **"ወክልና"** ማለት ተወካይ የተባለ አንድ ሰው ወካይ ለተባለው ሌላ ሰው እንደራሴ ሆኖ አንድ ወይም ብዙ ህጋዊ ሥራዎችን በወካዩ ሥም ለማከናወን ግዴታ የሚገባበት ውል ነው፤

12) **"ወካይ"** ማለት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 የተመለከቱትን የመጋዘን ተግባራት በመጋዘን ወኪሉ አማካኝነት የሚያስፈፅም አምራች፣ አቅራቢ፣ ገዥ፣ ላኪ፣ ተገበያይ ወይም አገናኝ አባል ነው፤

13) **"የመጋዘን ወኪል ወይም ወኪል"** ማለት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 የተመለከቱትን የመጋዘን ተግባራትን እንዲያከናውን ከወካይ ወክልና የተቀበለ ሰው ነው፤

14) **"ናሙና ማለወስድ"** ማለት ወደ ምርት ገበያ ማከማቻ መጋዘን የቀረበውን ወይም በግዥ ምክንያት ከማዕከላዊ ምርት ማከማቻ መጋዘን የሚወጣውን ምርት የጥራት ደረጃ ለመወሰን በተሚጠው የናሙና ማሚጫ ስልት መሠረት ወካይ የሆነ ምርሜ የሚወሰደበት አሠራር ነው፤

15) “**የደረጃ ማስወቂያ ቅፅ**” ማለት ወደፊት በሚወሰን ቀን ለሚደረግ ሽያጭ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ መጋዘን የገባ ምርት ተገቢው ምርመራ ከተደረገለት በኋላ በምርት ገበያው የጥራት ምርመራ ማዕከል የተሰጠው የጥራት ደረጃ ማገለጫ የምሥክር ወረቀት ነው፤

16) “**የምርት ገቢ ደረሰኝ**” ማለት የኢትዮጵያ ምርት ገበያ መጋዘኖች ወደ ምርት ማከማቻ መጋዘኑ የገባውን የምርት ማጠንና የጥራት ደረጃውን የሚገልፅት ደጋፊ ሰነዶች ትክክለኛነት ከተረጋገጠ በኋላ በመጋዘኑ አስተባባሪ፣ በመጋዘን ስራዎች ሱፐር ቫይዘርና በአቅራቢው ወይም በወኪሉ ተፈርሞ በሰነዶቹ የተጠቀሰው ምርት በመጋዘኑ ገቢ ስለመሆኑ በጊዜያዊ አስረጂነት ለአቅራቢው የሚሰጥ ሰነድ ነው፤

17) “**የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ**” ማለት የምርት ገበያው የሌላ ሰው ዕቃ ሚከቡን የሚረጋገጥበት በአዋጅ ቁጥር 372/96 መሠረት የተዘጋጀ የጽሑፍ ማስረጃ ሲሆን የኤሌክትሮኒክ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝንም ይጨምራል፤

18) “**የርክክብ ማስታወቂያ**” ማለት ገዥው በምርት ገበያው ግዥ የፈፀማበት ምርት ከሚገኝበት መጋዘን ወጪ ሆኖ እንዲሰጠው የሚያስችል በማዕከላዊ የምርት ማከማቻ መጋዘኑ የሚዘጋጅ ሰነድ ነው፤

19) “**የምርት ማስረከቢያ ማስታወሻ**” ማለት ገዥው በምርት ገበያው ግዥ የፈፀማባትን ምርት ከሚገኝበት መጋዘን ወጪ ሆኖ ለመወሰዱ የሚያረጋግጥ በማዕከላዊ የምርት ማከማቻ መጋዘኑ የሚዘጋጅ ሰነድ ነው፤

20) “**የዲሲፕሊን ክስ**” ማለት በዚህ መመሪያ ወኪሉ እንዲፈጽማቸው የተደነገጉትን የሚደረግ ግዴታዎች ወይም እንዳይፈፅማቸው የተከለከሉትን ያለሚደረግ ግዴታዎችን ተላልፏል በሚል የሚቀርብ ክስን ይመለከታል፤

21) “**የሥነ ምግባር ቁጥጥር ኮሚቴ ወይም ኮሚቴው**” ማለት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17 መሠረት የሚቋቋመና በመጋዘን ወኪሎች ላይ የሚቀርቡ የዲሲፕሊን ጉዳዮችን አይቶ ውሳኔ ለማስጠት ሥልጣን የተሰጠው ኮሚቴ ነው፤

22) “**የጥቅም ግጭት**” ማለት የመጋዘን ወኪሉ በወክልናው መሠረት ለወካዩ ወይም ለተለያዩ ወካዮቹ በአገልግሎት አሰጣጥም ሆነ በመረጃ አቀባበል ረገድ የሚያከናውነው ተግባር የአንዱን ወይም የሌላውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የሚጎዳ ወይንም ተጽእኖ የሚያሳድር ሆኖ ሲገኝ ነው፤

23) “**የመጋዘን ሥራዎች ሱፐርቫይዘር**” ማለት የማከማቻ መጋዘን ሥራዎችን እንዲመራ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ በመጋዘን ደረጃ የተመደበ ሰው ነው፤

(24) “**የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ**” ማለት በየትኛውም ቦታ የሚገኝ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ቅርንጫፍ ጽ/ቤትን በኃላፊነት እንዲመራ የተመደበ ሰው ነው፤

25) “**የቤተሰብ ወኪል**” ማለት አያትን፣ አባትን፣ እናትን፣ ልጅን፣ ወንድምን፣ እህትን ወይም የትዳር ጓደኛን በመወከል የሚሠራ የመጋዘን ወኪል ነው፤

26) “**ሰው**” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

27) በዚህ መመሪያ ወስጥ በወንድ ጾታ የተገለፀው ሴትንም ይጫለከታል፡፡

## 3. **የመመሪያው የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በአንቀጽ 7 የተመለከቱትን የማዘን ተግባራትን በወክልና በሚሠሩ ወኪሎች እና እነዚህን ተግባራት በራሱ በሚያከናወን ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለወኪሎች የምዝገባ ሥርዓት

## 4. **ወክልናን የማስመዝገብ ግዴታ**

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 የተዘረዘሩትን የማዘን ተግባራት እንዲያከናወን ወክልና የተሰጠው ወኪል ሥራ ከመጀመሩ አስቀድሞ የወክልና ማስረጃወን ሥራወን በሚያከናወንበት የምርት ገበያ ማዘን አቅርቦ ወክልናወን ካላስመዝገበ በስተቀር የማዘን ተግባራትን ማከናወን አይችልም፡፡

## 5. **የወካይ ግዴታዎች**

1/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 የተዘረዘሩትን የማዘን ተግባራት እንዲያከናወን ወክልና የሚሰጥ ወካይ ወክልናው ሥልጣን ባለው የፌደራል ወይም የክልል መንግሥታዊ አካል እንዲጸድቅ ማድረግ አለበት፡፡

2/ የማዘን አገልግሎትን ለማግኘት ወክልና የሚሰጥ ወካይ የሚሾመው ወኪል፡ -

(ሀ) ስለምርት ገበያው የማዘን አገልግሎትና ስለሚጠበቅበት ሥራ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው የሚያደርግ፣

(ለ) ከማዘን ወኪል የሚጠበቁትን ግዴታዎች ለማሟላት ተገቢው ብቃት ያለው መሆኑን፣

(ሐ) መልካም ሥነ ምግባር ያለወና የምርት ገበያወን ደንቦች አክብሮ ለመሥራት የሚችል መሆኑን፣ የሚረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡

## 6. **መዝገብ ስለማደራጀትና ምዝገባ ስለማከናወን**

1) ምርት ገበያው በእያንዳንዱ የምርት ማከማቻ ማዘን ወኪሎችን የሚመዘገብበት መዝገብ ወይም ኤሌክትሮኒክ የመረጃ ቋት ያደራጃል፣ ወኪሎችን ይመዘግባል፡፡

2) የሚያደራጀውም መዝገብ ወይም ኤሌክትሮኒክ የመረጃ ቋት በእያንዳንዱ የማዘን ወኪል ሥም የተዘጋጀና ከዋናው መዝገብ ጋር ማጣቀሻ ያለው አባሪ ማኅደር ይኖረዋል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው መሠረት ከእያንዳንዱ ወካይ አንጻር የሚከናወነው የወክልና ምዝገባ በየዓመቱ መታደስ ይኖርበታል፡፡ የመጋዘን ወኪሉ የዕድሳቱ ጊዜ ያለቀበትን ወካይ በተመለከተ በምርት ገበያው መጋዘን ማንኛውንም ዓይነት አገልግሎት መስጠት አይችልም፡፡

4) የምርት ገበያው የምርት ማከማቻ መጋዘን ሠራተኛ የወክልናው ሰነድ እንዲመዘገብ ተወካዩ ጥያቄ ሲያቀርብ ወክልናውን ከመመዝገቡ በፊት፡-

(ሀ) ወክልናው ለወኪሉ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 የተመለከቱትን የመጋዘን ተግባራት ብቻ ለማከናወን የሚያስችለው መሆኑን፣ እና

(ለ) የምርት ገበያው በተመሳሳይ ወኪል ቢያዙ የጥቅም ግጭት ሊያስከትሉ ይችላሉ በማለት የሚያወጣቸውን የወክልና ዓይነቶች መሠረት በማድረግ ወኪሉ የሚቀበለው ወክልና አስቀድሞ ከተሰጠው ወክልና ጋር የጥቅም ግጭት ሊያስከትል የሚችል መሆኑን፤ ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

## ክፍል ሶስት
## በወኪሎች ስለሚከናወኑ ተግባራትና አገልግሎት አሰጣጥ

### 7. በወኪሎች ስለሚከናወኑ ተግባራት

1) የመጋዘን ወኪሎች በምርት ገበያ ምርት ማከማቻ መጋዘን የሚያከናውኗቸው የመጋዘን ተግባራት የሚከተሉት ናቸው፡-

(ሀ) ወካዩ ወደ ምርት ገበያው እንዲገባለት የላከውን ምርት ወደ ምርት ገበያው የምርት ማከማቻ መጋዘን የማስገባት፣

(ለ) ለምርቱ ጥራት ደረጃ ለማውጣት ይቻል ዘንድ የምርቱን ናሙና የማስወሰድ እና የወካዩ ድርሻ የሆነውን የማመሳከሪያ ናሙና የመረከብ፣

(ሐ) የምርት ጥራት ደረጃ የማውጣት ሂደቱን የመከታተልና በእርጥበትና በሌሎች ምክንያቶች የጥራት ደረጃ ለወጣለት ሳይችል ሲቀር ምርቱን በምርት ገበያው መጋዘን ግቢ ወስጥ እንዲደርቅ በማድረግ ለዳግም ልኬትና የጥራት ምርመራ የማቅረብ፣

(መ) ስለምርቱ ጥራት ደረጃ ከወካዩ ጋር በመነጋገር በምርት ገበያው በተሰጠው የጥራት ደረጃ የሚስማማ ከሆነ በምርት ገበያው በሚዘጋጀው የደረጃ ማሳወቂያ ቅጽ ላይ የመፈረም፣ ወካዩ በጥራት ደረጃው ላይ ቅሬታ ሲኖረው የቅሬታ ፎርም በመሙላት ቅሬታውን በወቅቱ የማቅረብ፣ እንዲሁም ከደረጃ በታች በመሆናቸው እንዲወጡ የሚወሰኑና ተመልሶ የመውጣት ክልከላ የሌለባቸውን ምርቶች የማውጣት፣

(ሠ) በሚዘጋጀው የምርት ገቢ ደረሰኝ ላይ ወካዩን በመወከል ከመጋዘን አስተባባሪው ወይም ከመጋዘን ስራዎች ሱፐርቫይዘር ጋር በመሆን መፈረምና የወካዩ ድርሻ የሆነውን ቅጅ የገቢ ደረሰኝ መቀበል፣ ስለመቀበሉም ለወካዩ ወዲያውኑ የማሳወቅ፣

(ረ) ለምርት ማጓጓዝ ሥራ የሚሆን ትራንስፖርት የማመቻቸት፣ እንዲሁም

(ሰ) የማዛን ተግባራትን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን የማከናወን፡፡

2) ወኪሉ በገዥ ወይም በሻጭ የተወከለ ሲሆን የወኪልናው ተግባር በዚህ አንቀጽ ከፊደል (ሀ_ሠ) የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆኖ፣ የርክክብ ማስታወቂያ ሲደርሰው በወካዩ ስም ግዥ የተፈፀመበትን ምርት የምርት ሚከቢያ ማስታወሻ በሚረም ምርቱ ከሚገኝበት የምርት ማከማቻ ማዛን የሚከብ፣ እንዲሁም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በፊደል (ረ) እና (ሰ) የተመለከቱትን ይጨምራል፡፡

3) የማዛን ወኪል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተመለከቱት ተግባራት ወጪ የተሰጠው ወኪልና በምርት ገበያው አይስተናገድም፡፡

4) የባለሥልጣኑን ዕውቅና አግኝቶ በመሥራት ላይ ያለ የመድረክ ወኪል በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 መሠረት የመመዝገብና መዝገብ የማያዝ ግዴታዎች ሳይኖሩበት የምርት ገበያ አባሉን በመወከል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ሥር የተመለከቱትን የማዛን ተግባራት ሊያከናውን ይችላል፡፡

5) የመድረክ ወኪል በምርት ገበያ ማዛኖች የማዛን ተግባራትን ሲያከናውን በአንቀፅ 10 የተመለከቱትን የሥነ ምግባር ደንቦች ማክበር አለበት፡፡

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተመለከተው ድንጋጌ ቢኖርም የመድረክ ወኪሉ የማዛን ተግባራትን ሲያከናውን በአንቀጽ 10 ሥር የተመለከቱትን ጥፋቶች ፈጽሞ ቢገኝ በምርት ገበያው ደንብ የበለጠ የሚያስቀጣ ድንጋጌ ከሌለ በቀር አግባብነት ባላቸው የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች መሠረት ሊከሰስና ሊቀጣ ይችላል፡፡

## 8. ወኪሎች ወኪልና ከመቀበላቸው በፊት ሊሟሉበት ስለሚገባቸው መርሆዎች

1) ማንኛውም የማዛን ወኪል አገልግሎት ለመስጠት ወኪልና ሲቀበል፡ -

(ሀ) በተለያዩ ወካዮቹ መካከል የጥቅም ግጭት የማያስከትል፣

(ለ) በማንኛውም አገልግሎት አሰጣጡ ላይ ማስተጓጎልንና መዘግየትን የማያስከትል፣

(ሐ) የወካዩ ግልፅ ፈቃድ ከሌለ በስተቀር ወኪልና የተቀበለበትን ሥራ ለሌላ ሶስተኛ ሰው በወኪልና በመስጠት የማያሠራ መሆኑን፣

(መ) ወኪሉ የኅብረት ሥራ ማህበር፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት ኅብረት፣ የቤተሰብ ወኪል ወይም ምርት ተረካቢ ወኪል ካልሆነ በስተቀር የተቀበላቸው ወኪልናዎች በሙሉ በአንድ ማዛን ብቻ የተወሰኑ መሆኑን፣ ሚረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከቱት ቢኖሩም አንድ የመጋዘን ወኪል በማንኛውም ሁኔታ በቀን ከ10 ጭነት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች በላይ፣ በዓመቱ ውስጥ ደግሞ ከ40 በላይ ወኪልናዎችን ሊቀበል አይችልም፡፡

3) የመጋዘን ወኪሉ ተቀጣሪ ወይም የኅብረት ሥራ ማኅበር ወይም የኅብረት ሥራ ማኅበራት ኅብረት ተወካይ ሲሆን የማኅበሩን ወይም የቀጣሪውን ግልፅ የጽሁፍ ፈቃድ በማቅረብ ያለተጨማሪ የወኪልና ፎርማሊቲ ተመዝግቦ በወኪልና ሊሠራ ይችላል፡፡

4) ባለሥልጣኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ የጥቅም ግጭት ሊያስከትሉ የሚችሉ የወኪልና ዓይነቶችን ይወስናል፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተመለከቱት የምርት ገበያው ከጊዜ ወደ ጊዜ የመጋዘን ወኪሎችን የሥራ አፈጻጸም እየገመገመ የጥቅም ግጭት የሚያስከትሉ ተጓዳኝ የወኪልና ዓይነቶችን፣ ወኪሉ ሊቀበል የሚገባውን የወኪልና መጠንና የሥራ ክልሉን አድማስ በጥናት ለይቶ እያቀረበና በባለሥልጣኑ እያስወሰነ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

## 9. የወኪሎች መዝገብ የመያዝ ግዴታ

የመጋዘን ወኪል ወኪልናውን ተቀብሎ ሥራ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ፡-

1) ለግብይት ስለተላኩት የወካዩ ምርቶች መጠን፣ የደረሰበትን ተሸከርካሪ፣ የደረሰበትን ቀንና ሰዓት፣ የምርቱ የጥራት ደረጃ ምርመራ የተጠናቀቀበትን ጊዜ፣ የጥራት ደረጃውን፣ እና ስለመላሰሉት የምርቱ እንቅስቃሴዎች፣ እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅ ትዕዛዞችን የሚቀበልበት ቋሚ መዝገብ ማዘጋጀትና የዕለት ተዕለት መረጃን መመዝገብ፣

2) በሚያደራጀው መዝገብ ወስጥ የተለያዩ ወካዮቹን መረጃ ለያይቶ የሚይዝበት ክፍል ማለየትና መመዝገብ፣

3) ከወካዮቹ የሚቀበላቸውን ትዕዛዞች እና ስለአገልግሎት ክፍያው አፈጻጸም በወቅቱ መመዝገብ፣

4) ስለመዝገብ አያያዙም ሆነ የወካዮች መረጃ በምርት ገበያው የሚመለከተው ኃላፊ ሲጠየቅ የማሳየት ግዴታ አለበት፡፡

5) ወኪሉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚያደራጀውን መዝገብ ቢያንስ ለአንድ ዓመት ጠብቆ ማቆየት አለበት፡፡

## 10. ወኪሎች ሊከተሏቸው የሚገቡ የሥነ ምግባር ደንቦች

የመጋዘን ወኪሎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን እና ምርት ገበያው በየጊዜው የሚያወጣቸውን ሌሎች የስነ ምግባር ደንቦች የማክበር ግዴታ ተጥሎባቸዋል፡-

(ሀ) ውክልናውን ለሚመለከተው የምርት ገበያው መጋዘን ማስመዝገብ፣

(ለ) በምርት ገበያው መጋዘን ባጅ ወይም ሌሎች መለያዎች መጠቀም፤

(ሐ) የውክልናውን ሰነድ በተጠየቀ ጊዜ የማሳየት፣

(መ) ሥራው እስኪጠናቀቅ በምርት ገበያው መጋዘን እና በሚዛን ቦታ በአካል መገኘት፣

(ሠ) ከምርት ገበያው የመጋዘን ሠራተኞች ጋር በሥርዓት የመነጋገርና ተግባብቶ የመሥራት፣

(ረ) የምርት ገበያው የምርት ማከማቻ መጋዘን የተለያዩ ምርቶችን ለማስተናገድ ያወጣውን ቅደም ተከተል አለመጣስ፣

(ሰ) በምርት ገበያው መጋዘን አደንዛዥ ዕፅ ወስዶ ወይም መጠጥ ጠጥቶ አለመግባት፣

(ሸ) በምርት ገበያው መጋዘን የጦር መሣሪያ ወይም ጉዳት የሚያደርስ ቁስ ይዞ አለመግባት፣

(ቀ) በምርት ገበያው መጋዘን ግቢና የሥራ አካባቢ ሁከት ወይም አምባጓሮ አለመፍጠር፣

(በ) የምርት ጥራት ደረጃ ለማስለወጥ ወይም የምርት ርክክብ ለማድረግ ከምርት ገበያው ሠራተኞች ወይም የግብይት ፈጻሚዎች ጋር በህገወጥ መንገድ አለመተባበር፣

(ተ) የተረከበውን ምርት ሌላ ደረጃ ካለው ተመሳሳይ ምርት፣ ወይም ከባዕድ ነገሮች ጋር የመቀላቀል ተግባር አለመፈፀም፤

(ቸ) ምርት የተረከበበትን ደረሠኝ ለምርት መረከቢያነት በድጋሚ በማቅረብ ለማሳሳት ያለመሞከር፣

(ኀ) ወደ ምርት መጋዘን ከገቡ በኋላ ከደረጃ በታች በመሆናቸው እንዲወጡ የተወሰነባቸውንና የመውጣት ክልከላ የሌለባቸውን ምርቶች ጥሎ ያለመሄድ፤

(ነ) በሥራው አጋጣሚ ያወቀውን ማንኛውንም የንግድ ምስጢር ለግብይት ፈጻሚዎች ወይም ለሶስተኛ ወገኖች አለመግለጽ፣

(ኘ) ከወካዩ ጋር የጥቅም ግጭት የሚያስከትል ወይም ሊያስከትል የሚችል ውክልና አለመቀበል፣

(አ) በውክልና ሰነዱ ከተመለከቱት የመጋዘን ተግባራት ውጪ ሌሎች ተግባራትን አለማከናወን፣

## 11. የማዛን ተግባራትን በራሳቸው ስለሚያከናውኑ አቅራቢና ገዥዎች፣ እና ስለቤተሰብ ወኪል

የማዛን ተግባራትን በራሱ የሚያከናውን ሰው፣ በዚህ መመሪያ ወስጥ የተመለከቱትን ሌሎች ድንጋጌዎች ማክበር ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በአንቀጽ 7 የተመለከቱትን ተግባራት ሲያከናውን፡-

1) በወኪሎች መዝገብ እንዲገባ አይደረግም፡፡

2) በአንቀጽ 10 (ሀ)፣ (ሐ)፣ (ኘ) እና (አ) ከተመለከቱት ድንጋጌዎች በስተቀር የተቀመጡትን ሌሎች የሥነ ምግባር ደንቦች ማክበር አለባቸው፡፡

3) በምርት ገበያው ደንብ የበለጠ የሚያስቀጣ ድንጋጌ ከሌለ በቀር በአንቀጽ 10 የተመለከቱትን የሥነ ምግባር ደንቦች ጥሰው የተገኙ አቅራቢዎች ወይም ገዥዎች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 21 የተቀመጡት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆኑባቸዋል፡፡

## ክፍል አራት
## ስለወክልና መቅረት፣ ወኪልን ስለማገድ ወይም ስለመሠረዝ

## 12. ወክልና ቀሪ ስለሚሆንባቸው ሁኔታዎች

ወክልናው በህግ የሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ለማዛን ወኪል የተሰጠ ወክልና፡-

1/ የማዛን ወኪሉ የፈፀመው ጥፋት በኮሚቴው ታይቶ ከወኪሎች መዝገብ እንዲሠረዝ ሲወሰን፤

2/ ወካዩ ከአባልነት ወይም ከግብይት ተሳታፊነት ሲሰረዝ፣ የወክልናው ሥራ ቀሪ ይሆናል፡፡

## 13. ወኪልን ከሥራ ስለማገድ

1) ማንኛውም የማዛን ወኪል በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 በፊደል (ሰ)፣ (ሸ)፣ (ቀ)፣ (በ)፣ (ተ)፣ (ቸ)፣ (ኀ)፣ (ነ)፣ (ኘ) እና (አ) ሥር ከተመለከቱት ተግባራት መካከል አንዱን ፈፅሟል ተብሎ ክስ ሲቀርብበትና ጉዳዩ በኮሚቴ ታይቶ ወሳኔ እስኪያገኝ ድረስ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 17 መሠረት በተቋቋመው ኮሚቴ ሰብሰቢ ዕገዳ ሊጣልበት ይችላል፡፡

2) ወካዩ በምርት ገበያው እንዳይሳተፍ የታገደ እንደሆነ ዕገዳው እስከሚነሳ ድረስ ወኪሉም የታገደውን ወካይ ሥራ ማከናወን አይችልም፡፡

**14. ዕገዳው ስለሚቆይበት ጊዜና የሚያስከትለው ውጤት**

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 መሠረት የተሰጠ የዕገዳ ትዕዛዝ በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን ከ15 ቀናት ሊበልጥ አይችልም፡፡

2) ኮሚቴው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ዕገዳ የተሰጠበትን ክስ በ15 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ማስጠት አለበት፡፡

3) ኮሚቴው በ15 ቀናት ወስጥ ወሳኔ ማስጠት ካልቻለ ዕገዳው ባይነሳም ወኪሉ ሥራውን እየሠራ ጉዳዩ እንዲታይ ይደረጋል፡፡

4) በማዛን ወኪል ላይ የሚጠው የዕግድ ትዕዛዝ በተቻለ ማጠን ወደ ምርት ማዛን ገብተው በሂደት ላይ የሚገኙ ምርቶች ለጉዳት የሚጋለጡበትን ወይም ወካዩ ንብረቱን ለማካታተል የሚቻልበትን ሁኔታ ከግምት ያስገባ መሆን ይኖርበታል፡፡

5) ምዝገባው የታገደበት የማዛን ወኪል ዕገዳው ፀንቶ ባለበት ጊዜ ወስጥ በልዩ ሁኔታ ፈቃድ ካልተሰጠው በስተቀር በማንኛወም የምርት ገበያው ማዛን የወክልና ተግባሩን ማከናወን አይችልም፡

## 15. የወኪሉን ማገድ ወይም መሠረዝ ለወካዩ ስለሚስታወቅ

1) ወኪሉ በአንቀጽ 13 መሠረት ሲታገድ ወይም በአንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ (3) (ሐ) መሠረት የወክልና ሥልጣኑ ሲሠረዝ ምርት ገበያው ወካዩ አባል ወይም የወካዩ አገናኝ አባል ስለወሳኔው እንዲያወቅ የወሳኔው ቅጂ ወዲያውኑ እንዲደርሰው ሚደረግ አለበት፡፡

2) ወኪሉ የተሠረዘበት ወካይ ሌላ ወኪል የመሾም መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

## 16. የወክልናው መሠረዝ የሚያስከትለው ወጤት

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 25 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ከመዝገብ የተሰረዘ ማንኛወም የማዛን ወኪል በሁሉም የምርት ገበያው ማዛኖች የወክልና ተግባሩን ማከናወን አይችልም፡

## ክፍል አምስት
## የዲሲፕሊን ክስ ስለሚቀርብበትና ስለሚስተናገድበት ሁኔታ

## 17. የሥነ ምግባርና ቁጥጥር ኮሚቴ ስለማቋቋም

1) በማዛን ወኪሎች ላይ የሚቀርበወን የዲሲፕሊን ክስ መርምሮ ወሳኔ የሚሰጥ አምስት አባላት የሚኖሩት የማዛን ወኪሎች የሥነ ምግባርና የቁጥጥር ኮሚቴ በእያንዳንዱ የምርት ገበያ ማዛን ይቋቋማል፡፡

2) ኮሚቴወም የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

(ሀ) የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ ….ሰብሳቢ

(ለ) የማዛኑ የአስተዳደር ሠራተኛ …ም/ሰብሳቢ

(ሐ) በማዛኑ የሚሠሩ የማዛን ወኪሎች ተወካይ …………አባል

(መ) በማዛኑ የሚቋቋመው የአቅራቢዎች ኮሚቴ ተወካይ …….አባል

(ሠ) በቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊው የሚመደብ ሠራተኛ......... .........አባልና ፀሐፊ ይሆናል፡፡

3) የሥነ ምግባር ቁጥጥር ኮሚቴው ስብሰባ በሰብሳቢው ወይም እርሱ በሚይገኝበት ጊዜ በምክትል ሰብሳቢው ሊጠራና ሊሰበሰብ ይችላል፡፡

4) በእያንዳንዱ የዲሲፕሊን ክስ የመጀመሪያ ስብሰባ ሰብሳቢውን እና የማዛን ወኪሎችን ተወካይ ወይም የአቅራቢዎችን ኮሚቴ ተወካይ ጨምሮ ሶስት የኮሚቴው አባላት ከተገኙ ምልዐተ ጉባዔ ይሆናል፡፡ ሆኖም በመጀመሪያው ስብሰባ ምልዐተ ጉባዔው ካልተሟላ በቀጣዮቹ ስብሰባዎች ሰብሳቢውን ጨምሮ ሶስት የኮሚቴው አባላት ከተገኙ ምልዐተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

5) ኮሚቴው ወሳኔ የሚሰጠው በደምፅ ብልጫ ሲሆን ድምፅ እኩል ለእኩል በተከፈለ ጊዜ ግን በሰብሳቢው ወይም ሰብሳቢው በሌለ ጊዜ በምክትል ሰብሳቢው ድጋፍ ያገኘው ሃሳብ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

6) የማዛን ወኪሎች ተወካይ በማዛኑ በሚሠሩ ወኪሎች ጠቅላላ ስብሰባ በቀጥታ ይመረጣል፡፡

7) የኮሚቴው አባል የዲሲፕሊን ጉዳዩ ከሚመለከተው የማዛን ወኪል ጋር የወክልና፣ የንግድ ግንኙነት፣ ፀብ፣ የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው እንደሆነ በራሱ ወይም በሌሎች ሰዎች ጥያቄ ሲቀርብ ጉዳዩን ማየት የለበትም፡፡ እንዲሁም የኮሚቴ አባል የዲሲፕሊን ክስ ሲቀርብበት ወይም በማናቸውም ምክንያት ሥራውን ሲለቅ አባሉን የወከለው አካል በምትኩ ሌላ ተወካይ መተካት አለበት፡፡

8) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ (ሐ) እና (መ) የተመለከቱት ተወካዮች የአገልግሎት ዘመን ሁለት ዓመት ነው፡፡ ሆኖም ለቀጣዩ የአገልግሎት ዘመን በድጋሚ ሊወከሉ ይችላሉ፡፡

## 18. የሥነ ምግባር ቁጥጥር ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር

1) በወኪሉ ላይ የቀረበውን ክስ መርምሮ ከባድ ወይም ቀላል የዲሲፕሊን ቅጣት መወሰን፣ ወይም ወኪሉ ከክሱ በነጻ እንዲሰናበት መወሰን፣ እንዲሁም
2) ወሳኔ ለመስጠት ይቻል ዘንድ ይረዳኛል ያላቸውን የሰነድ ማስረጃዎች ወይም ምስክሮች አስቀርቦ የመመርመር ሥልጣን አለው፡፡

## 19. የዲሲፕሊን ግድፈት ሚፈፀማ ስለ ማሳወቅና ክስ ስለማቅረብ

1) ማንኛውም የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ፣ አቅራቢ፣ የማዛን ወኪል ወይም ሌላ በማዛን ወኪል ላይ ቅሬታ አለኝ የሚል ማንኛውም ሰው በአንድ የማዛን ወኪል ላይ ይህን መሚያ ተላልፏል በሚል በፅሁፍ አቤቱታ ባቀረበ ጊዜ የአባላትና የደንበኞች ግንኙነት ሱፐርቫይዘር አቤቱታ አቅራቢው የክስ ቅፅ እንዲሞላ ሚድረግ አለበት፡፡

2) የአባላትና የደንበኞች ግንኙነት ሱፐርቫይዘር ጉዳዩ በስነ ምግባርና የቁጥጥር ኮሚቴው ታይቶ ውሳኔ እንዲያገኝ ወዲያውኑ ለኮሚቴው ሰብሳቢ ወይም እርሱ በሌለበት ጊዜ ለም/ሰብሳቢው ያቀርባል፡፡

3) በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 10 የተመለከቱት ጥፋቶች ስለመፈፀማቸው የሚያውቅ ወይም በነዚህ ጥፋቶች ምክንያት በማዘን ወኪሉ በደል ደርሶብኛል የሚል ማንኛውም ሰው ማንነቱን አሳውቆ ወይም ሳያሳውቅ ቅሬታውን በማዘኑ ለሚገኘው የአባላትና የደንበኞች ግንኙነት ሱፐርቫይዘር ሊያመለክት ወይም ጥቆማ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ መሠረት ጥቆማ የደረሰው የአባላትና የደንበኞች ግንኙነት ሱፐርቫይዘር ቅሬታውን ወይም ጥቆማውን በማጣራት በወኪሉ ላይ ክስ ሊቀርብበት የሚገባው መሆኑን ሲያምን የጥፋቱን ሁኔታና ማስረጃዎቹንም በመግለፅ በወኪሉ ላይ ክስ እንዲመሠረት ጥቆማውን በተቀበለ ከሁለት የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ወስጥ ለኮሚቴው ሰብሳቢ ወይም እርሱ በሌለበት ጊዜ ለም/ሰብሳቢው ማቅረብ አለበት፡፡

5) የማዘኑ የአባላትና የደንበኞች ግንኙነት ሱፐርቫይዘር ቅሬታዬን በአግባቡ አያስተናግድልኝም ብሎ የሚያምን አሚልካች በማዘን ወኪሉ የተፈፀመውን ጥፋት ከማስረጃ ጋር በቀጥታ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ኃላፊ በማቅረብ ጉዳዩ እንዲታይለት ሊደረግ ይችላል፡፡

## 20. የቀረበውን ክስ ስለማጣራትና ውሳኔ ስለመስጠት

ኮሚቴው ክሱን ሲያጣራና ውሳኔ ሲሰጥ በሥነ ሥርዓት ህጎች የተቀመጡትን ድንጋጌዎች መከተል ሳይገደድ የሚከተሉትን ደንቦች ሥራ ላይ ያውላል፡-

1) ተከሳሹ ለቀረበበት ክስ መልስ እንዲሰጥ መጥሪያ ይልክለታል፣
2) ተከሳሹ የቀረበበትን ክስ ያመነ እንደሆነ በእምነቱ መሰረት ውሳኔ ይሰጣል፣
3) ተከሳሹ ክዶ የተከራከረ እንደሆነ ቃሉን ይቀበላል ማስረጃ መስማት አስፈላጊ ሆኖ ካገኘውም አስቀርቦ ይሰማል፣
4) ተከሳሹ ጉዳዩን ለመስማት በተቀጠረበት ቀን ያልቀረበ እንደሆነና መጥሪያው በአግባቡ የደረሰው መሆኑ ከተረጋገጠ እርሱ በሌለበት ክሱን ይሰማል፣
5) ኮሚቴው በቀረበው ክስ ላይ ውሳኔ ሲሰጥ ፍትሕንና ርትዕን መሠረት ያደርጋል፡፡

## 21. ስለዲሲፕሊን ጥፋቶች እና ስለቅጣታቸው

### 1) የዲሲፕሊን ጥፋቶች፡-

(ሀ) በተከሳሾች የሚፈፀሙት ጥፋቶች ከባድ ወይም ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋቶች ተብለው የሚፈረጁ ሲሆን በአንቀጽ 10 ከፊደል (ሀ)-(ረ) የተመለከቱትን መተላለፍ ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋቶች ሲሆኑ በፊደል (ሰ)፣ (ሸ)፣ (ቀ)፣ (በ)፣ (ተ)፣ (ቸ)፣ (ኀ)፣ (ነ)፣ (ኘ) እና (አ) የተገለፁትን መተላለፍ ደግሞ ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋቶች ናቸው፡፡

(ለ) በቀላል የዲሲፕሊን ጥፋቶች የተቀጣ ወከል በ18 ወራት ወስጥ በሌላ ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋት ተከሶ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ለከባድ የዲሲፕሊን ጥፋቶች በተቀማጡት ቅጣቶች ይቀጣል፡፡

**2) በቀላል የዲሲፕሊን ጥፋቶች ስለሚጣለው ቅጣት፡ –**

ጥፋተኛ የተባለ ተከሳሽ የፈፀመው ጥፋት ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋት ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ኮሚቴው በቅደም ተከተል፡ –

(ሀ) የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ፣

(ለ) ከብር 3,000 (ሶስት ሺህ ብር) የማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ሊወስን ይችላል፡፡

**3) በከባድ የዲሲፕሊን ጥፋቶች ስለሚጣለው ቅጣት፡-**

i/ ጥፋተኛ የተባለ ተከሳሽ የፈፀመው ጥፋት ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ሆኖ ጥፋቱ የመጀመሪያና በማስጠንቀቂያ ሊታለፍ የሚችል መሆኑን ኮሚቴው ሲያምን ኮሚቴው በቅደም ተከተል፡ –

(ሀ) በጽሑፍ ማስጠንቀቂያ፣

(ለ) ከብር 3,001 (ሶስት ሺህ አንድ ብር) እስከ ብር 10,000 (አሥር ሺህ ብር) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከአንድ ወር እስከ ሶስት ወር በሚደርስ ዕገዳ፣

(ሐ) ከመዝገብ እንዲሠረዝ ሊወስንበት ይችላል፡፡

ii/ ኮሚቴው የተከሳሹ ጥፋት አደገኛና የግብይት ሥርዓቱ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል መሆኑን ሲያምን ከዚህ በላይ የተማለከተወን ቅደም ተከተል ሳይጠበቅ የመጨረሻወን ቅጣት ሊወስንበት ይችላል፡፡

4/ በኮሚቴው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 (ለ) እና 3 (ለ) ሥር የሚወድቅ ወሳኔ የተሰጠበት የማዘን ወከል ቅጣቱን ሳይፈፅም ወደ ሥራው መማለስ አይችልም፡፡

**22. ስለይግባኝ**

1/ ኮሚቴው በሰጠው ወሳኔ ቅሬታ ያለው ወሳኔው በተሰጠው በ30 ቀናት ወስጥ ይግባኙን ምርት ገበያው ለሚከይመው አካል ማቅረብ ይችላል፡፡

2/ ምርት ገበያው የሚከይመው አካል በኮሚቴው የተሰጠዋን ወሳኔ መርምሮ ሊያጸናው፣ ሊያሻሽለው ወይም ሊሽረው ይችላል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት በሚሰጠው ወሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ሰው ወሳኔው በተሰጠው በ30 ቀናት ወስጥ ይግባኙን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይችላል፡፡

4/ ባለሥልጣኑ በዚህ ጉዳይ ላይ የሚሰጠው ወሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

## ክፍል ስድስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 23. ይርጋ

በዚህ መመሪያ መሠረት በወኪል ላይ የሚቀርብ ክስ ወኪሉ ፈጽሟል የተባለው ድርጊት ከተፈፀመ ወይም ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ ዓመት ወስጥ በአንቀጽ 19 መሠረት ክስ ካልቀረበበት ከተጠቀሰው ጊዜ በኋላ ክስ ሊቀርብበት አይችልም፡፡ ሆኖም በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን ድርጊቱ ከተፈጸመበት ጊዜ ጀምሮ ከሁለት ዓመት በኋላ ክስ ሊቀርብበት አይችልም፡፡

### 24. እንደገና ወደ ሥራ ስለመመለስ

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ /3/ (ሐ) መሠረት ከማዝገብ እንዲሠረዝ የተወሰነበት ወኪል ወደ ማዛዘን ወኪልነት ሥራ መመለስ የሚችለው ወሳኔው ተፈጻሚ ከሆነ ከሶስት ዓመት በኋላና በሌላ የኢኮኖሚ ጉዳይ ተከሶ ያልተቀጣ መሆኑ በምርት ገበያው ሲረጋገጥ ነው፡፡

### 25. የምርት ገበያው ኃላፊነት

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ይህን መመሪያ ለማስፈፀም፡ –

1) ከባለድርሻ አካላት ጋር ወይይት በሚድረግ የግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ያከናወናል፣
2) ሁሉም የምርት ማዛዘኖች የወኪሎችን ምዝገባ ለማከናወን የሚችሉበትን አሠራር ይዘረጋል፣
3) ለምርት ገበያው ሠራተኞች የተሟላ ሥልጠና የማስጠት፣ የወኪሎችን ምዝገባ ማከናወንና በመመሪያው መሠረት ሥራቸወን የመከታተልና የመደገፍ ሥራ ያከናወናል፣
4) በምርት ማዛዘን አካባቢ ለመስናና ብልሹ አሠራር በር የሚከፍቱ አሠራሮችን ያስወግዳል፣
5) የሥነ ምግባርና ቁጥጥር ኮሚቴወን ያደራጃል፣ የአሠራር ሥርዓቱን ይደግፋል፣ እንዲሁም በኮሚቴው የተሰጡ ወሳኔዎችን ያስፈፅማል፣
6) ለዲሲፕሊን ኮሚቴ አባልነት የሚሚጠው የማዛዘን ወኪሎች ተወካይ በዲሲፕሊን ኮሚቴ አባልነቱ በሚንቀሳቀስበት ወቅት በመደበኛ ሥራው ላይ በደል የሚደርስበትን ሁኔታ በማዛኑ ከሚሠሩ ወኪሎች ጋር በመመካከር ያመቻቻል፡፡
7) መመሪያወን በመተግበር ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን በማጥናት የባለስልጣኑን ቅድሚያ ፈቃድ በማግኘት የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣
8) በየምርት ማዛዙ ስለሚዛገቡ የማዛዘን ወኪሎች ሚጃዎች በየወሩ ለምርት ገበያ ባለስልጣን ሪፖርት ያቀርባል፣

## 26. የምርት ገበያ ባለሥልጣኑ ኃላፊነት

ባለሥልጣኑ የመመሪያውን አፈጻጸም የመቆጣጠር ሥልጣኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፦ -

1) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ስለመመሪያው ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ይሠራል፣
2) የወከልና ቅጽ፣ የአገልግሎትና የክፍያ ሞዴል ወሎች ያዘጋጃል፣
3) የምርት ገበያው መጋዘኖች የወኪሎችን ምዝገባ ለማከናወን የሚችሉበትን አሠራር ማዘርጋቱን ይከታተላል፣
4) የመመሪያውን አፈጻጸም ይገመግማል፣ ባጋጠሙ ችግሮች ላይ አስፈላጊ የሆነ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡

## 27. የማሸጋገሪያ ድንጋጌ

1) ቀደም ሲል የተሰጠው ወክልና የማዘን ተግባራትን ብቻ ለማከናወን የሚል ቢሆንም መመሪያው ከጸናበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ወስጥ ለሚሠራበት መጋዘን ወኪሉ አቅርቦ ካላስመዘገበ በስተቀር የወክልና ሥራውን ሊያከናወን አይችልም፡፡
2) ቀደም ሲል የተሰጠው ወክልና ከዚህ መመሪያ ጋር ያልተጣጣመ ከሆነ መመሪያው ከጸናበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ወስጥ እንዲስተካከል በማድረግ ወኪሉ አቅርቦ ካላስመዘገበ በስተቀር የወክልና ሥራውን ሊያከናወን አይችልም፡፡

## 28. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ ሊሻሻል ይችላል፡፡

## 29. መመሪያው ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከየካቲት 1 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት 1 ቀን 2005 ዓ.ም**

**የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን ቦርድ**